በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ
PHARMACEUTICALS FUND AND SUPPLY AGENCY

# የግዥ ትንበያ እና የገበያ ጥናት ሥራ መመሪያ

## 384/2013

ነሐሴ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**እንቀጽ** **የአንቀጽ ርዕስ** **ገጽ**


**መግቢያ** 3

**የመመሪያው ዓላማ** 3

**ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ** 4

አጭር ርዕስ 4

ትርጓሜ 4

የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን 5

መርሆዎች 5

**ክፍል ሁለት፡- የሙያ ስነ-ምግባር** 7

**ክፍል ሶስት፡- የግዥ ትንበያ እና የአቅርቦት እቅድ ተግባራት** 10

የመደበኛ መድኃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች ግዥ ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድ 10

በጤና ተቋማት ዓመታዊ የመድኃኒት ምጠና 10

የኤጀንሲው ቅርንጫፎች ከጤና ተቋማት የሚቀርብ የመድኃኒት ጥያቄ መረጃ አያያዝ እና አደረጃጀት 11

በማዕከል የግዥና የአቅርቦት እቅድ አዘገጃጀት እና አወሳሰን 12

የጤና ፕሮግራም መድኃኒቶች ትንበያ እና የግዥ ዕቅድ አዘገጃጀትና አወሳሰን 14

ካፒታል የህክምና መሳሪዎች መስፈርት ዝግጅትና የግዥ ጥያቄ አቀራረብ መማሪያ 15

በአስቸኳይ ምላሽ ለሚሹ የጤና ችግሮች የህክምናና ተዛማጅ ግብዓቶች ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድን ማዘጋጀት 15

**ክፍል አራት፡- አስቸኳይ የግዢ ጥያቄ ተግባራት** 17

አስቸኳይ የግዥ ጥያቄ የሚሹ ሁኔታዎችና አተገባበር መመሪያ 17

**ክፍል አምስት፡- የክምችትና አቅርቦት ክትትል ተግባራት** 19

የመድኃኒት ክምችት አስተዳደርና ከፍተኛና ዝቅተኛ የክምችት መጠን አወሳሰን 19

የህይወት አድን መድኃኒቶች እና ሌሎች መድኃኒቶች አቅርቦትና የክምችት ይዞት ክትትል 19

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦት ክትትል 20

**ክፍል ስድስት፡- የገበያ ጥናት ተግባራት** 21

**ክፍል ሰባት፡ የክትትልና ግምገማ ስርዓት** 22

**ክፍል ስምንት፡ ልዩ ልዩ ጉዳዮች** 23



FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency

# የግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት መመሪያ

የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 553/99 በተቋቋመውና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 12/2 ና 12/5 መሰረት የኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ የኤጀንሲውን የአፈጻጸም መመሪያዎችን መርምሮ እንዲያጸድቅ በተሰጠው ስልጣን ይህ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች የግዥ ትንበያ እና የገበያ ጥናት መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

## 1. መግቢያ

የበሽታዎች መከላከልና የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ እንዲሆን ቀጣይነት ያለው የመድኃኒት አቅርቦት የላቀ ድርሻ አለው፡፡ ይህን ለማሳካት የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ለጤና ተቋማት ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ መሰረታዊ መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያቀርብ በአዋጅ ቁጥር 553/99 የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ ተቋቁሟል፡፡

የመሰረታዊ መድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የማድረስ ስራ በአስተማማኝ መሰረት ላይ እንዲቆም የመድኃኒት አመራረጥ፣ መጠን አወሳሰን፣ግዥ፣ ክምችት አስተዳደር እና የመድኃኒት አጠቃቀም አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ሲሆን ይገባል፡፡

የግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት በአገሪቱ የሚገኙ ጤና ተቋማትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን የግዥ ጥያቄ በማዘጋጀት ለመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ግዥ የስራ ሂደት ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም ያለው የክምችት ይዞት በሚፈለገው መጠን እንዲሆን የክምችት ክትትል ስራዎችን ያከናውናል፡፡

ስለሆነም በስራ ሂደቱ የሚከናወኑ ስራዎችን ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ለማሳየት ፤ በተለያየ ደረጃ ከግዥ ትንበያና ከገበያ ጥናት ጋር ተሳትፎ ያላቸው የኤጀንሲው እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሲኖራቸው የሚገባውን የእርስ በርስ የስራ ግንኙነት በሁሉም ወገኖች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ለማስቻል ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የመመሪያው ዓላማ

አንድ ወጥና ግልጽ የሆነ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦት አስተዳደር ስርዓት እንዲኖር፡-

- የጤና ተቋማትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ውጤታማና ወቅታዊ የሆነ የመድኃኒቶች መረጣና ምጠና ማካሄድ
- መረጃ ላይ የተደገፈ የህይወት አድንና የመሠረታዊ መድኃኒቶች የግዥ ዝርዝር ማዘጋጀት በተጨማሪም
- የገበያ ጥናት ስራዎችን በማከናወን በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ መሠረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ማረጋገጥ፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኢጀንሲ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች የግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት መመሪያ" ተብሎ ይጠራል።
**384/2013**

## 4. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰተው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1. **"መድኃኒት"** ማለት በሽታን ለመመርመር፣ ለመከላከል፣ ለማስታገስ ወይም ለማከም የሚያገለግል ማንኛውንም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የሕክምና መገልገያዎችንና መሳሪያዎችን ይጨምራል። በዚህ መመሪያ ላይ " መድኃኒት" ተብሎ የተጠቀሰው የሕክምና መገልገያዎች፣ መሳሪያዎችን እና ኬሚካሎችንና ሪኤጀንቶችን ይጨምራል።

2. **"የሕክምና መገልገያ"** ማለት በሽታን ለመመርመር ወይም ለማከም በውስጥ ወይም በውጭ የሰውነት አካል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውንም መገልገያ ሲሆን፣ የቁስል መስፊያ ክሮችን፣ ስሪንጆችን፣ መርፌዎችን፣ ፋሻ፣ ጎዝ፣ ጥጥ እና መሰል ዝግጅቶችን፣ የራጅ ፊልሞችን ወ.ዘ.ተ ይጨምራል።

3. **"የላቦራቶሪ ኬሚካልና ሪኤጀንት"** ማለት በሽታን ለመመርመር፣ ጥናቶችን ለማካሄድና የበሽታዎችን ሂደት ለመከታተል የሚውል ማንኛውንም ንጥረ ነገሮችን ያካትታል።

4. **"የህክምና መሳሪያ"** ማለት በሽታን ለመመርመር ወይም ለማከም ከውስጥ ወይም በውጭ የሰውነት አካል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውንም መሳሪያ ሲሆን የተለያዩ የመመርመሪያ፣ የላቦራቶሪ፣ የቀዶ ጥገና እና የጥርስ ህክምና መሳሪያዎችን ወ.ዘ.ተ ይጨምራል።

5. **"ካፒታል ህክምና መሳሪያ"** ማለት በሽታን ለመመርመር ወይም ለማከም የሚውል ማንኛውንም መሳሪያ ሲሆን በመጠን ጥቂት፣ ከፍተና ዋጋ የሚይዙና ለረጅም ግዜ አገልግሎቶት ሚሰጡ (MRI machine, X-ray machine, CD4 machine...) ሲሆኑ የተለያዩ የመመርመሪያ፣ የላቦራቶሪ፣ የቀዶ ጥገና እና የጥርስ ህክምና መሳሪያዎችን ወ.ዘ.ተ ይጨምራል።

FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply

6. **“አማካይ ወርሃዊ ፍጆታ”** ማለት አንድ መድኃኒት በአማካይ በወር ውስጥ ምን ያህል እንደተሰራጨ ወይም ስህሙማን እንደታደለ የሚያመለክት መጠን ነው፡፡ መጠኑን ለማስላት አንድ መድኃኒት ሳለፋት ቅርብ ተከታታይ ወራት የተሰራጨውን ጠቅላላ መጠን ለተሰራጨበት ወራት በማካፈል ይወሰናል፡፡

7. **“የመጠባበቂያ የክምችት መጠን”** ባልተጠበቀ የፍጆታ መጨመር ፣ የአቅርቦት ጊዜ ከተጠበቀው በላይ መዘግየት እና በተለያዩ ሁኔታዎች ምክንያት በድንገት ለሚከሰት የክምችት መሳሳት ሊያገለግል የሚችል የክምችት መጠን ነው፡፡

8. **“ዝቅተኛ የክምችት መጠን”** ማለት በኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፎች ወይም በጤና ተቋማት ሊኖር የሚገባው ዝቅተኛ የክምችት መጠን ሲሆን፣ ክምችቱ ከዚህ በታች እንዳይሆን ክትትል ለማድረግ ይጠቀማል፡፡ ይህ መጠን በአቅርቦት ጊዜ ክምችትና በመጠባበቂያ የክምችት መጠን ሊሸፈን የሚችል ነው፡፡

9. **“ከፍተኛ የክምችት መጠን”** ማለት በኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፎች ወይም በጤና ተቋማት ሊኖር የሚገባው ከፍተኛ የክምችት መጠን ሲሆን፣ ክምችቱ ከዚህ በላይ እንዳይኖር ክትትል ለማድረግ ይጠቀማል፡፡ ይህ መጠን በማንኛውም ወቅት ሊኖር የሚገባውን ዝቅተኛ የክምችት መጠንና የአቅርቦት ጊዜ ሰሌዳ ክምችት መጠን የሚሸፍን ነው፡፡

10. **“የግዥ ትንበያ”** ማለት ስተገላባጭ ፈንድና ጤና ፕሮግራሞች የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎችን የጤና ተቋማት ፍላጎትን ታሳቢ በማድረግ የተለያዩ የምጠና ዘዴዎችንና መረጃዎችን በመጠቀም ለተወሰነ የጊዜ ቆይታ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎችን በመጠንና በዋጋ ማስላት ነው፡፡

11. **“የአቅርቦት እቅድ”** ማለት የግዥ ትንበያ ከተሰራ በኋላ በክምችት፣ በጨረታ ሂደት እና በመንገድ ላይ ያለውን ከግምት ውስጥ በማስገባት መቅረብ ያለበትን መጠንና የአቅርቦት ሰሌዳ መወሰን ማለት ነው፡፡

12. **“የክምችት ክትትል”** ማለት በማእከላዊና በቅርንጫፍ መጋዘኖች ውስጥ ያለውን የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎችን ክምችት፣ በጨረታ ሂደት እና በመንገድ ላይ ያለውን መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባትና አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ የአቅርቦት ክፍተት እንዳይፈጠር ማድረግ ነው፡፡

13. **“ማእከላዊ’** ማለት የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤትና በስሩ የሚተዳደሩ መጋዘኖች ማለት ነው፡፡

14. **“ቅርንጫፎች”** ማለት ኤጀንሲው የመድኃኒት አቅርቦትና ተዛማጅ የስራ መስተጋብሮችን ከጤና ተቋማት፤ ክልል ጤና ቢሮዎች፤ ዞን ጤና ‘መምሪያዎች፣ ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶችና ሌሎችም አካላት ጋር የሚከናውንበት የስራ ሂደት ነው፡፡

15. “የገበያ ጥናት” ማለት የገበያ ስጋቶችን በተደራጀና መረጃን መሰረት ባደረገ መልኩ በመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ ውጤታማና ቀልጣፋ የገበያ ሁኔታ በመፍጠር የመድሃኒቶች የዋጋ ተደራሽነት የማረጋገጥ ስርዓት ነው::

16. “እስቾኪዴ ግዥ ጥያቄ” ማለት ከተለመደው ግዥ ሂደት በተለየና ፈጣን በሆነ መንገድ ግዥ እንዲከናወን የሚቀርብ ጥያቄ ማለት ነው::

## 5. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የኤጀንሲው ቅርንጫፎችና ዋናው መስሪያ ቤት ለሚያከናውናቸው ማናቸውም በግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት ስራዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል

## 6. መርሆዎች

የግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት ተግባራት ለሚከተሉት መርሆዎች ተገዥ ይሆናል::

- አገልጋይነት (serving customer)
- ቁርጠኝነት (Commitment)
- ሙያዊ ስነ ምግባር (Professionalism)
- ልህቀት (Excellence)
- እውቅና (recognition)
- በጋራ መስራት (team work)

# ክፍል ሁለት

## 7. የሙያ ስነ-ምግባር

የመድኃኒት የህክምና መገልገያዎች የግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት መመሪያ የመከተለውን የሙያ ስነ-ምግባር ያካትታል፡፡

### 1. ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት /Responsibility for Impact/

ስራው ለተቋሙ የሚያስፈልገውን የመድሃኒት፣የህክምና መግልገያዎችነና መሳሪያዎችን በትክክለኛው አይነትና መጠን መተንበይ፣ግዥ ዕቅድ ማዘጋጀና የገበያ ቀኝት ማካሄድ ሲሆን ስራዉ በተገቢው ጥራትና መጠን ካልተከናወነ፣ የጤና ችግርና የሀብት ብክነትን ያመጣል፤ በጤና ተቋሙ በሚገለገሉ ተገልጋዮች ቅሬታን በመፍጠር በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡

### 2. ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ

በእለት ተእለት የስራ ሂደት ኤጀንሲውን የሚገልፁ መረጃዎችን፣ በግዥ ሂደትና ሌሎችም ጉዳዮች በሚስጥር መያዝ ያለባቸው ሲሆን እነዚህ ሚስጥሮች ያለአግባብ በማይገባቸው እጅ ቢገቡ በደንበኛ ላይ አድልዎ በማድረስ የስነ ልቦና እና ማህበራዊ ግንኙነቱን ያዛባል፡፡ በተጨማሪም በመድሃኒት አስተዳደር ሂደቱ ላይ የመልካም አስተዳደር እጦትን ያስከትላል፡፡

### 3. ፈጠራ

በግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት ጋር በተገናኙ መረጃ የመሰብሰብ፣የመተንተንና የማሰራጨት ስራ፤ የመድሀኒት አያያዝና አስተዳደር ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ አዳዲስ ሃሳቦችንና የአሠራር ዘዴዎችን በማመንጨት የሥራው ውጤታማነት እንዲሻሻል ማድረግን ይጠይቃል፡፡

### 4. የሥራ ግንኙነት /Work Communication/

ከቅርብ ሃላፊው፣ ከስራ ክፍሉ ባለሙያዎች፣ ከውስጥ ሰራተኞች፣ ከጤና ባለሙያዎች፣ ከተቋሙ ሰራተኞች ጋር የውስጥ ግንኙነት የሚያደርግ ሲሆን ከውጭ ከመድሀኒትና የህክምና መገልግያዎችና

ግብአቶች አቅራቢዎች፣ ከታካሚዎችና ከተማሪዎች ጋር፤ የሚኖረው ግኑኝነት ሙያዊ ስነ-ምግባርን ባከበር መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

የስራ መመሪያ ለመቀበልና ሪፖርት ለማድረግ፣ ሙያዊ እገዛ ለማግኘትና ለመስጠት፣ ለመመካከር፣ መረጃ ለመቀበልና ለመስጠት፣ ለማስተማርና ለማሰልጠን፣ የመድሃኒት የህክምና አገልግሎት ለመስጠትና ለማማከር በከፍተኛ ተነሳሽነትና ቅንነት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

## 5. ኃላፊነት ለንብረት

ስራውን ለማከናወን የሚጠቀምባቸው እንደ ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር፤ ጠረጴዛ፤ መቀመጫ ወንበር የፋርማሲ መጻህፍት፣ መድሃኒቶችና የመገልገያ ግብአቶችና የመሳሰሉትን ወጪያቸው ንብረቶችን ተረክቦ በጥንቃቄ መያዝ ይጠበቅበታል፡፡

## 6. ጥረት

የተቋማትን የመድሃኒት ፍላጎት በአይነትና በመጠን ማስላት እንዲሁም ካለው በጀት ጋር በማጣጣም፣የመድሃኒት አቅርቦት ሂደቱ በአግባቡ እንዲሄድ ማድረግ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን መቀነስ እንዲሁም መከታተል፣ ስታስቲካዊ ትንተናዎችን ማጠቃለል እና በተለያዩ የስራ አይነቶች ውስጥ የማይመሳሰሉ ነገሮች ሲያጋጥም የመተንተንና በመረጃ የተደገፈ አስታራቂ ሃሳቦችን ማመንጨት ነው፡፡

ስራው ትዕግስትን የሚፈታተኑ በመድሃኒት ግዥ ወቅት ከተለያዩ ክፍሎችና አቅራቢዎች የሚያጋጥም አለመግባባት፣ የበጀት፣ አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣምና ከሌሎች አካላት ጋር በሃሳብ መጋጨትና መከራከር እንዲሁም ከስራው ባህሪ አንፃር የሚመጣ ስነ ልቦናዊ ጫና የሚያጋጥምበት ሥራ ነው፡፡ ይህንን ተቋቁሞ ስራውን ውጤታማ ለማድረግ ትዕግስትንና በተረጋጋ ስሜት መስራትን ይጠይቃል፡፡

FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency
Office of Board of Directors

# ክፍል ሶስት

# የግዥ ትንበያ እና የአቅርቦት ዕቅድ ተግባራት

## 8. የመደበኛ መድሃኒቶች ግዥ ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድ አዘገጃጀትና አወሳሰን

### 1. በጤና ተቋማት ዓመታዊ የመድኃኒት ምጠና

1.1 የኤጀንሲው የመድኃኒት ግዥ እቅድ ከመንግስት ጤና ተቋማት የሚቀርብ በበጀት የተደገፈ የአቅርቦት ፍላጎትን መሰረት ያደርጋል፡፡

1.2 ጤና ተቋማት የአካባቢያቸው የጤና ችግር እና ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ወቅቱን የጠበቀ የመድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች መዘርዝር በተቋሙ ውስጥ ባሉ መድኃኒትና ህክምና ኮሚቴዎች አማካኝነት እንዲያዘጋጁ ከባለድርሻ አካላት ጋር ይሰራል፡፡

1.3 በተራ ቁጥር 1.2 በተገለፀው የጤና ተቋማት መዘርዝርና በአገሪቱ የመድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን የተዘጋጀውን የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች መዘርዝር መነሻ በማድረግ ለዓመታዊ የመድኃኒት ትንበያ የሚውል የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች መዘርዝርና ወቅታዊ ዋጋን በማካተት ያዘጋጃል፡፡

1.4 በተ.ቁ. 1.3 የተገለጸውን መዘርዝር በሚመለከተው አካል አፀድቆ እስከ ነሐሴ 30 ድረስ በቅርንጫፎች በኩል ለጤና ተቋማት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

1.5 ጤና ተቋማት የተገለጋዩን ህዝብ ብዛት ፣ የበሽታ ዓይነት፣ የአጠቃቀም ፍጆታ ፣ የአገልግሎት መረጃ እንዲሁም ያላቸውን በጀት መሰረት በማድረግ ለአመት የሚያስፈልጋቸውን የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች የትንበያውን መዘርዝር በመጠቀም በመጠንና በዋጋ በማስላት እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፡፡

1.6 ጤና ተቋማት በፍጆታ መረጃ መሰረት ዓመታዊ የመድኃኒት አቅርቦት ጥያቄ በሚያዘጋጅበት ወቅት አቅርቦት ያልነበረበት ግዜ (Stock out period)፣ ያለፉ ጊዜያት ፍጆታ፣ የጤና አገልግሎት ሽፋን ለውጥ ታሳቢ በማድረግ እንዲሁም የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

1.7 የኤጀንሲው ቅርንጫፎች በጤና ተቋማት ትንበያው በጥራት እንዲከናወን ከወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች፣ ዞን ጤና መምሪያዎችና ከክልል ጤና ቢሮዎች የሚመለከታቸው ሙያተኞች ጋር በመሆን የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ::

1.8 የመንግስት ጤና ተቋማት ዓመታዊ በውል ስምምነት የታሰረ የመድኃኒት አቅርቦት ጥያቄ በአቅራቢያቸው ለሚገኝ የኤጀንሲው ቅርንጫፍ በተሰጣቸው ቅጽ መሰረት በጤና ተቋማት የመድኃኒትና ህክምና ኮሚቴ ፀድቆ በተቋሙ ኃላፊ ተፈርሞ እስከ ህዳር 30 ቀን ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

1.9 በተ.ቁ 1.8 የተገለጸውን የአቅርቦት ጥያቄ ከጤና ተቋሙ ዓመታዊ የመድኃኒት በጀት ጋር የተጣጣመ ሲሆን ይገባል::

## 2. የኤጀንሲው ቅርንጫፎች ከጤና ተቋማት የሚቀርብ የመድኃኒት ጥያቄ መረጃ አያያዝ እና አደረጃጀት

2.1 የኤጀንሲው ቅርንጫፎች ከጤና ተቋማት በበጀት ተደግፈው የቀረቡ ዓመታዊ የግዥ ጥያቄዎችን እስከ ህዳር 30 ቀን ድረስ ይሰበስባሉ::

2.2 የቅርንጫፉ የግዥ ትንበያና የአቅርቦት እቅድ ቡድን ከጤና ተቋማት የሚቀርበውን ጥያቄ ያጠናቅራል ይተነትናል::

2.3 በተ.ቁ 2.2 የተገለጸውን የጤና ተቋማት የመድኃኒት ፍላጎት ከሚመለከታቸው የቅርንጫፉ የስራ ክፍሎች ጋር በመገምገም ረቂቅ ትንበያን ያዘጋጃል::

2.4 በግዥ ትንበያ ቡድን አስተባባሪነት ሌሎች ባለ ድርሻ አካላትን ያካተተ ግብረ ሃይል በማቋቋም በተ.ቁ 2.3 የተገለጸውን ረቂቅ የመድኃኒት ፍላጎት በመገምገም የመጨረሻ ትንበያ ያዘጋጃል::

2.5 የኤጀንሲው ቅርንጫፎች በውል ስምምነት የታሰረ የመድኃኒት አቅርቦት ጥያቄ ካቀረቡት ጤና ተቋማት በተጨማሪ አዲስ የሚቋቋሙ መንግስታዊ ጤና ተቋማት ፍላጎትን ፤ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ጤና ተቋማት በግል አስመጪና አከፋፋይ ሊቀርብላቸው ያልቻለውን የመድኃኒት ፍላጎት በዓመታዊ ትንበያው ማካተት ይኖርባቸዋል::

2.6 ጤና ተቋማት ዓመታዊ የመድኃኒት ፍላጎታቸውን በአግባቡ መተንበይ እስከሚችሉ (ይህን ለማከናወን አቅም እስኪፈጥሩ) የኤጀንሲው ቅርንጫፎች የተመረጡ ጤና ተቋማት ፍላጎት መሰረት በማድረግ ለሌሎች ተመሳሳይ ጤና ተቋማትም ጭምር የአቅርቦት ፍላጎት መተንበይ ይኖርባቸዋል::

2.7 የቀጣዩን በጀት ዓመት የግዥ ሂደት በተገቢ ጊዜ ለመጀመር እንዲቻል ቅርንጫፎች ያጠናቀሩትን በውል ስምምነት የታሰረ የጤና ተቋማት አመታዊ የመድኃኒት ፍላጎት ትንበያና የግዢ ጥያቄ ከማዕከል በተላከው ቅፅ መሰረት ለግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት እስከ ታህሳስ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ መላክ ይጠበቅባቸዋል::

## 3. በማዕከል የግዥና የአቅርቦት እቅድ አዘገጃጀት እና አወሳሰን

3.1 የማዕከል የግዢ ትንበያና የገበያ ጥናት ቡድን ከቅርንጫፎች የተላከውን የፍላጎት ትንበያና የግዢ ጥያቄ በአራት አይነት ክፍፍል (መድኃኒት፣ የህክምና መሣሪያ፣ የላቦራቶሪ ሬኤጀንቶችና የህክምና መገልገያዎች) ለየብቻው በመለየት ያጠናቅራል::

3.2 የተጠናቀረውን የፍላጎት ትንበያ መረጃ የማዕከል የመደበኛ መድኃኒቶች የግዢ ትንበያና የአቅርቦት እቅድ ቡድን ካለፉት ጊዜያት ፍጆታና ከቅርንጫፎች የፍላጎት ትንበያ ንፅፅር አንፃር በማየት ይተነትናል::

3.3 የተጠናቀረውን መረጃ ከዋናው መስሪያ ቤት፣ ከኤጀንሲው ቅርንጫፎች እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት የምክክር አውደ ጥናት በማዘጋጀት በአስተያየት እንዲዳብርና የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝበት ያደረጋል::

3.4 የማዕከል የክምችት ክትትልና ግዥ ትንበያ ቡድን ያለፉት ጊዜያት ፍጆታ፣ የአቅርቦት ክፍተት፣ በማዕከል መጋዘኖች በክምችት የሚገኝ፣ በጨረታ ሂደት እና በመንገድ ላይ ያለውን የክምችት መጠን መረጃ ያጠናቅራል::

3.5 በተራ ቁጥር 3.3 የተመለከተውን ጥቅል የግዢ ጥያቄ በተራ ቁተር 9.3.4 ከተጠናቀረው መረጃ ጋር በማጣጣም በቀጣይ እንዲገዛ የሚፈለገው መጠንና በበጀት ያሰላል ካለው የፋይናንስ አቅም አንፃር ይገመግማል::

3.6 የፋይናንስ አቅም የተሰላውን በጀት መሸፈን ካልቻለ አስፈላጊው ማስተካከያ ይደረጋል:: የሚደረገው ማስተካከያም ሕይወት አድንና መሰረታዊ የሆኑ መድኃኒቶችንና የህክምና መገልገያዎችን በማስቀደም አሳሳቢ ሳልሆኑ የጤና ችግሮች ማከሚያ የሚሆኑትን በመቀነስ (VEN/ABC reconcilation) የሚሰራ ይሆናል::

3.7 በግዥ ትንበያ እና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት የተጠናቀረውን ጥቅል የግዢ ጥያቄ መጠን ፣ ዋጋ እና የአቅርቦት ሰሌዳን ባካተተ መልኩ እስከ ጥር 30 ለመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ግዥ የስራ ሂደት ያስተላልፋል:: የመጨረሻ ግዥ ጥያቄ ከመውጣቱ በፊት ከቅርንጫፎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የምክክር አውደ ጥናት ይካሄዳል::

3.8 በተራ ቁጥር 3.7 እንደተገለፀው በመረጃ ተደግፎ የተተነበየው የግዥ ጥያቄ ለኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ እንዲፀድቅ ይደረጋል:: የግዢ ጥያቄው ካልፀደቀ ወደ ግዢ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት ተመልሶ በተሰጠው አስተያየት መሰረት የሚስተካከል ይሆናል::

3.9 በተራ ቁጥር 3.8 የፀደቀው የግዥ መጠን የኤጀንሲውን ቅርንጫፎች ማዕከል ባደረገ መልኩ ጥቅል የስርጭት ዕቅድ (Distribution Plan) ተዘጋጅቶ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ስርጭት የስራ ሂደትየስራ ሂደት እንዲያውቀው ይደረጋል:: ይህም በቀጣይ ለሚደረገው ስርጭት መነሻ ይሆናል::

3.10 የግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት ለግዥ ቀርቦ አግባብ በሆነ የግዥ ስልት የሚቀርበውን መጠን ከወቅታዊ የክምችት ይዘትና ከእያንዳንዱ መድኃኒት ተፈላጊነት አንፃር ክትትል ያደርጋል:: በዚህም መሰረት በትንበያ ወቅት ታሳቢ ከተደረገው በተፃራሪ ተፈላጊነታቸው የጨመረ ወይም የቀነሰ መድኃኒትና የህክምና መገልገያዎችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለግዥ የስራ ሂደት በወቅቱ ያሳውቃል::

3.11 ደንበኞች ከመደበኛው የግዥ ጥያቄ ውጭ መጠይቅ ሲያቀርቡ ለምሳሌ ወረርሽኝ ሲነሳ ለድንገተኛ የግዥ ጥያቄ በጤና አገልግሎት ከሚኖረው ወሳኝ ሚና አንፃር ታይቶ ተገምግሞ ለግዥ የስራ ሂደት ይቀርባል::

3.12 በየዓመቱ የሦስት ዓመት ትንበያና የአንድ ዓመት የግዥ ዕቅድ የሚዘጋጅ ሲሆን በአመቱ የሚደረገው የግዥ ትንበያ ባለፋት ዓመታት ለበጀት ዓመቱ የተተነበየውን መጠን እንደ ግብአት ይጠቀማል::

## 9. የጤና ፕሮግራም መድኃኒቶች ትንበያ እና የግዥ ዕቅድ አዘገጃጀትና አወሳሰን

1. የጤና ፕሮግራምሞች መድኃኒቶች ትንበያና የግዥ ዕቅድ ለማከናወን የግዥ ትንበያና አቅርቦት እቅድ ቡድን የሚያስተባብራቸው ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጡ አባላትን ያቀፈ ቴክኒካል ቡድን (Quantification Technical Working Group) እንዲቋቋም ያደርጋል::

2. ቡድኑ የትንበያውን አጠቃላይ አካሄድ፣ የመረጃ ምንጭ፣ የምጠና ዘዴ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ያስቀምጣል::

3. የምክክር አውደ ጥናት በማዘጋጀት አጠቃላይ ሂደቱ ላይና ታሳቢ ሊደረጉ የሚችሉ ነጥቦች ላይ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት ጥልቀ ውይይት ይደረጋል:: በውይይቱ የስምምነት ነጥቦችን መሰረት በማድረግ የተለያዩ የምጠና ዘዴዎችን እና አጋዥ ሶፍትዌሮችን በመጠቀምና እንደየ ፕሮግራሙ ተጨባጭ ሁኔታ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ትንበያና የአንድ ዓመት የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል::

4. የተዘጋጀው ትንበያ እና የአንድ ዓመት የግዥ እቅድ በሚመለከተው አካል እንዲመጸድቅ ይደረጋል:: እንደአስፈላጊነቱም ከመጽደቁ በፊት ለባለድርሻ አካላት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና የጋራ ግንዛቤ ሊፈጠርበት ይገባል::

5. የፀደቀው የአንድ ዓመት የግዥ እቅድ የአቅርቦት እቅድ ተዘጋጅቶለት ለግዥ የስራ ሂደት ይተላለፋል:: በተጨማሪም የስርጭትና ሌሎችም የሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች የአቅርቦት ዕቅዱን እንዲያውቀው ያደርጋል::

6. ለግዥ የተላለፈው ዓመታዊ የግዥ ጥያቄ ከወቅታዊ የክምችት ሁኔታና ከእያንዳንዱ መድኃኒት ተፈላጊነት አንፃር ክትትል ያደርጋል:: በዚህም መሰረት በምጠና ወይም በትንበያ ታሳቢ ከተደረጉት በተጓራሪ ተፈላጊነታቸው የጨመረ ወይም የቀነሰ መድኃኒቶችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለግዥ የስራ ሂደት ይቀርባል::

7. እንደየ ፕሮግራሙ ተጨባጭ ሁኔታ ለአንድ ዓመት የተሰራው የፍላጎት ትንበያ ታሳቢ የተደረጉትን ጉዳዮች ባገናዘበ መልኩ በየስድስት ወሩ ይከለሳል::

## 10. ካፒታል የህክምና መሳሪያዎች መስፈርት ዝግጅትና የግዥ ጥያቄ አቀራረብ መማሪያ

1. የህክምና መሳሪያዎች የግዥ ፍላጎት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል ጤና ቢሮ እና ከጤና ተቋማት የግዥ ጥያቄ ለግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት ይቀርባል::

2. በተ.ቁ 10(1) የቀረበውን የህክምና መሳሪያ መስፈርት በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን መመሪያ ግምት ውስጥ በማስገባት ይገመግማል:: በግምገማው ውጤት መሰረት ከጠየቀው አካል ጋር በመነጋገር መስፈርቱን ይከልሳል::

3. በተስተካከለው መስፈርትና የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ከጠያቂው አካል ጋር በፅሁፍ የአቅርቦት ውል ይገባል::

4. በውሉ መሰረት የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት የግዥ ጥያቄ ለመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ግዥ የስራ ሂደት ያቀርባል::

## 11. በአስቸኳይ ምላሽ ለሚሹ የጤና ችግሮች የህክምናና ተዛማጅ ግብዓቶች ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድን ማዘጋጀት

1. በአገር አቀፍ ደረጃ በጤናው ዘረፍ በሚቋቋመው የዝግጁነትና ምላሽ ግብረ ሃይል የሚሳተፍ ባለሙያ ይመደባል::

2. የሚመደበው ባለሙያ ለጤና ችግሮች ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ የህክምናና ተዛማጅ ግብዓቶችን መዘርዝር ከግብረ ሃይሉ ጋር በመሆን ያዘጋጃል::

3. የሚመደበው ባለሙያ በጤና ግብዓት አቅርቦት ላይ የሚሰሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተወጣጣ ንዑስ ኮሚቴ እዲቋቋም ያደርጋል ኮሚቴውን ያስተባብራል::

4. በኤጀንሲው ስራውን ለማስተባበር በሚያመች አግባብ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች የተውጣጣ ኮሚቴ እንዲዋቀር ያደርጋል ወይም ስራውን በቅርብ የሚከታተል ባለሙያ ይመድባል::

FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency

5. በተ.ቁ 11(3) በተጠቀሰው ንዑስ ኮሚቴ አማካኝነት ለተለዩት የጤና ችግሮች ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ የህክምናና ተዛማጅ ግብዓቶችን ትንበያን የግዥ እቅድ ዝግጅት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል:: ከዚህ በታች የተዘረዘሩትና ሌሎችም አስፈላጊ መረጃዎች መሰብሰብ ይኖርባቸዋል::

5.1 ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮች ጋር ተያያዥ መረጃዎች (የችግሩን ስፋት፣ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍል በህሪ፣ ችግሩ የሚሸፍና ጊዜ...ወ.ዘ.ተ)

5.2 በኤጀንሲውና ዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ መጋዘንች ያለውን የክምችት መጠን ይለያል

5.3 በኤጀንሲውና በተለያዩ አካላት በግዥ ሂደት ያለውን መጠንና የመቅረቢያ ግዜ ይለያል

5.4 በመንግስትና አጋር ድርጅቶች ለችግሩ ምላሽ የመደቡትን ሀብት/በጀት መጠን ይለያል

5.5 በተ.ቁ 11.5.2 እና 11.5.3 ከተጠቀሰው በተጨማሪ የአቅርቦት እቅድ ለማዘገጀት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል::

6. የተሰበሰበውን መረጃና የባለ ሙያዎችን አስተያየት መነሻ በማድረግ ጥቅል ፍላጎትን ይተነብያል፤ በተለያዩ አካላት በክምችትና በግዥ ሂደት ያለውን መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ መቅረብ ያለበትን ይለያል፤ የአቅርቦት የግዜ ሰሌዳ ያዘጋጃል እንዲሀም የግዥ ስልትን ያመላክታል::

7. የተለየውን ተጨማሪ ፍላጎት ከበጀት ምንጩ ጋር በማጣጣም ለግብረ ሃይሉ በማቅረብ ያፀድቃል የፀደቀውን የግዥ ዕቅድ መሰረት ግዥ መጀመሩን ይከታተላል::

8. ክምችትን ይከታተላል፣ ግብረ ሃይሉ በሚያስቀምጠው የግዜ ሰሌዳ ቢያንስ በየሳምንቱ በመደበኛነት የክምችት ይዘት ሪፖርት ለግብረ ኃይሉና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል እንዲሁም መፈጸማቸውን ይከታተላል::

9. በኤጀንሲው የስራ ክፍሎች ከተቋቋመው ከሚቴ/ከተመደቡ ባለሙያዎች ጋር በመሆን በተቀመጠው አግባብ የግዥና የስርጭት ስራዎች መፈፀማቻን ይከታተላል፣ የችግሩን ወቅታዊ ሁኔታ በማገናዘብ እንደአስፈላጊነቱ ትንቢያውንና የግዥ እቅዱን ይከልሳል::

# ክፍል አራት

# አስቸኳይ የግዥ ጥያቄ ተግባራት

## 12. አስቸኳይ የግዥ ጥያቄ የሚሹ ሁኔታዎችና አተገባበር

1. አስቸኳይ የግዥ ጥያቄ አስገዳጅ ሁኔታዎች

   1.1 በመጋዘን እንዲሁም በግዥ ሂደት ላይ ያለ ክምችት በጥራት ተቆጣጣሪ አካል አግልግሎት ላይ እንዳማይውል ከተረጋገጠ፤ በግዚያውነት ጥቅም ላይ እንዳይውል ከታገደ ፣ በውስጥ የጥራት ደረጃ መመዘኛ መስፈርት በግዚያውነት ወይም እስከመጨረሻው ጥቅም ላይ እንዳማይውል ከተወሰነ እና ለአገልግሎት ብቁ ሆኖ ካልተገኘ

   1.2 በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ክምችት ከባከነ

   1.3 በውስጥ አሰራር ክፍተት የክምችት እጥረት ከተከሰተ (ማሳሰቢያ፡ የክፍተቱ ምክኒያት ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል)

2. አስቸኳይ የግዥ ጥያቄ አተገባበር

   2.1 በተራ ቁጥር 12.1 ስር በተጠቀሱት ምክንያቶች የተፈጠረ የክምችት ክፍተት መለየትና በሌላ የተሻለ አማራጭ ክፍተቱ መሞላት ካልተቻለ የግዥ እቅድ ማዘገጀት እና አስቸኳይ የግዥ ጥያቄ ይቀርባል::

# ክፍል አምስት

# የክምችትና አቅርቦት ክትትል ተግባራት

## 13. የመድኃኒት ክምችት አስተዳደርና ከፍተኛና ዝቅተኛ የክምችት መጠን አወሳሰን

1. በኤጀንሲው ቅርንጫፎች መጋዘኖች እና በመንግስታዊ ጤና ተቋማት የሚገኘውን የክምችት መጠን ለመገምገም ከሚያገለግሉ አመላካቾች (Indicators) ውስጥ ከፍተኛና ዝቅተኛ የክምችት መጠኖች፣ የመጠባበቂያ የክምችት መጠን፣ አማካይ ወርሃዊ ፍጆታ እና አቅርቦት የሚወስደው ጊዜ ይገኙበታል፡፡

2. በኤጀንሲው ማዕከላዊና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እና በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት ጥቅም ላይ የሚውሉ መድኃኒቶች የእያንዳንዳቸው ከፍተኛ እና ዝቅተኛ የክምችት መጠን የግዥ ሲሊዳን፣ ለማቅረብ የሚወስደውን ግዜ፣ የመጋዘኖች የማከማቸት አቅም (Storage Capacity) እና የፍጆታ መረጃን መሰረት በማድረግ ይወሰናል፡፡ ይህም በየጊዜው ወቅታዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 14. የህይወት አድን መድኃኒቶች እና ሌሎች መድኃኒቶች አቅርቦትና የክምችት ይዘት ክትትል

1. ኤጀንሲው የጤና የመድኃኒት ፖሊሲዎችን፣ አገር አቀፉን የመድኃኒት መዘርዝር፣ የህክምናና አሰጣጥ መመሪያዎችንና (STGs) ሌሎችንም ተዛማጅ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በጤናው ዘርፍ መጥፋት የሌለባቸውን ሕይወት አድን መድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡ የሕይወት አድን መድኃኒት (Vital drugs & related supplies) አቅርቦት የተሟላ እንዲሆን ልዩ ትኩረት ይደረጋል፡፡

2. ወርሃዊው የክምችት ክትትል ሪፖርት ለሁሉም የጤና ፕሮግራሞችና በመደበኛ ለሚቀርቡ የህይወት አድን መድሃኒቶች ይጠናቀራል፡፡

3. በማዕከል ያለው የመረጃ ሥርዓት እስኪጠናከር እና መረጃዎችን ከአንድ ምንጭ ማግኘት እስከሚቻል የኤጀንሲው ቅርንጫፎች ሕይወት አድን መድኃኒት ክምችት አንድ ወጥ በሆነ የሪፖርት ቅጽ በመጠቀም ወር በገባ በ27ኛው ቀን በማጠናቀር ለማዕከል የግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት ያቀርባሉ፡፡

4. የማዕከል የግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት ከቅርንጫፎች የደረሰውን እና በማዕከል መጋዘኖች እንዲሁም በግዥ ሂደት የሚገኘውን ሕይወት አድን መድኃኒቶች ክምችት በአንድ ላይ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል እንዲሀም የክምችት ክትትል ሪፖርት ያዘጋጃል።

5. በተራ ቁጥር 14.3 የተጠናቀረው ሪፖርት የአቅርቦት ሁኔታ በፐርሰንት ይሰላል፣ የአቅርቦት ክፍተት ለሚታይባቸው የመድኃኒት ዓይነቶች ምክንያቱን በማጥናት አቅርቦቱ የሚሻሻልበትን መንገድ ያመቻቻል፣ ከአንድ ቅርንጫፍ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ ወይም ከማእከል ወደ ቅርንጫፎች መዛወር ያለባቸውን ክምችቶች በተመለከተ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችና ቅርንጫፎች ጋር በመነጋገር ዝውውሩን ያመቻቻል ፣ ሪፖርት እና ትንተናውን ለበላይ አካላትና ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ወሩ በገባ እስከ 5 ቀን ያቀርባል።

6. ከህይወት አድን መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ዝርዝር ውጪ ያሉ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች የክምችት ሁኔታ በቅርንጫፎች፣ በማዕከል መጋዘኖች እንዲሁም በግዥ ሂደት ያለውን ክምችት ከግምት ውስጥ በማስገባት በየሦስት ወሩ (በየሩብ ዓመቱ) ሪፖርት ይጠናቀራል፤ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችና ለበላይ አካላት ለክትትልና ለአፈፃፀም ይቀርባል።

7. የኤጀንሲው ቅርንጫፎች በተገላባጭ መድኃኒት ፈንድና በጤና ፕሮግራም የሚቀርቡ መድኃኒቶችንና የህክምና መገልገያዎች በየሩብ ዓመቱ የክምችት መጠናቸውን በመገምገም ከፍተኛ ክምችት ያላቸውን፣ አዝጋሚ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ፣ በቅርንጫፉ የማይፈለጉ ክምችቶችን፣ የአቅርቦት እጥረት የታየባቸውን፣ የጊዜ ገደባቸው በመቃረቡ ምክንያት ወደ ሌላ ቅርንጫፍ መዛወር የሚያስፈልጋቸውን መድኃኒቶች እና በሩብ ዓመት ውስት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ መድኃኒቶች ዓይነት እና መጠን በዝርዝር ለዚሁ በተዘጋጀ ቅፅ በማስፈር ለግዥ ትንበያና የገበያ ጥናት የስራ ሂደት ይልካሉ።

8. የማዕከል የክምችት ክትትልና የአቅርቦት እቅድ ቡድን በ.ተ.ቁ 14.6 ከቅርንጫፎች የቀረበውን ሪፖርት ያጠናቅራል።

9. በተራ ቁጥር 14(7) የተጠናቀረው ሪፖርት መነሻነት ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ ቢዛወሩ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የክምችት ዓይነቶችን ከሚመለከታቸው ቅርንጫፎች እና ከማዕከላዊ የክምችት እንዲሁም የስርጭት የስራ ሂደት ጋር በመነጋገር የክምችት ዝውውሩን ያመቻቻል። በተጨማሪም የችግሩን ምክንያት በመመርመር ዘለቄታዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል።

FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency

10. በተራ ቁጥር 14(7) እና 14(8) የተጠናቀረው ሪፖርት ለኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር፣ ለግዥ የሥራ ሁደት፣ ለክምችትና ስርጭት የስራ ሂደት እንዲሁም ለፕላን፣ ክትትልና ግምገማ የስራ ሂደት እንዲደርሳቸው ይደረጋል::

## 15. በሀገር ውስጥ የሚመረቱ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦት ክትትል

1. በተራ ቁጥር 8 በተገለፀው አግባብ በተገላባጭ ፈንድ የሚቀርቡ መድኃኒቶች አመታዊ ትንበያ ከተጠናቀቀ በኋላ ከዚህ ውስጥ በሃገር ውስጥ የሚመረቱ መድኃኒቶች በዓይነትና በመጠን በመለየትና በዋጋ በማስላት ለግዥ የስራ ሂደት ይቀርባል::

2. በግዥ የስራ ሂደት በኩል የጨረታ ሂደቱ ተጠናቆ አቅራቢው ከታወቀ በኋላ ከግዥ የስራ ሂደት የግዥ ትዕዛዝ የወጣላቸውን መድኃኒቶች በመቀበል ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ የሚደርሰውን መጠን ከፋፍልና የአቅርቦት የጊዜ ሰሌዳ በመስራት ለአቅራቢዎች፣ ለቅርንጫፎች እና ለክምችትና ስርጭት የስራ ሂደት ይልካል::

3. የሃገር ውስጥ አምራቾች በተሰጣቸው የግዥ ትዕዛዝና የዘቅርቦት ጊዜ ማቅረባቸውን ለመለካት በየሩብ ዓመቱ የኤጀንሲው ቅርንጫፎች የአገር ውስጥ የመድኃኒት ፋብሪካዎች/አቅራቢዎች የአቅርቦት አፈፃፀም አጠናቅረው እንዲልኩ ይደረጋል::

4. የክምችት ክትትልና አቅርቦት እቅድ ቡድን ከቅርንጫፎች የተላከውን የአቅርቦት አፈፃፀም ሪፖርት በማጠናቀርና በየፋብሪካዎች የሚቀርበውን የአቅርቦት አፈፃፀም ሪፖርት መሰረት በማድረግ ከሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች ማህበር ጋር የኤጀንሲው ኃላፊዎች በተገኙበት የጋራ የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአቅርቦት አፈፃፀማቸውና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ግምገማ ያደርጋል::

5. በአፈፃፀም ደካማ የሆኑ (በተሰጣቸው የጊዜ ሠሌዳ ማቅረብ ያልቻሉ) የሀገር ውስጥ አምራቾች በተመለከተ ተገቢው የእርምት እርምጃ ይወሰዳል::

FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency
Office of Board of Directors

# ክፍል ስድስት

# የገበያ ጥናት ተግባራት

## 16. የገበያ ጥናት ተግባራት

1. በኤጀንሲው የሚቀርቡ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ከገለና ከሌሎችም አቅራቢዎች አንጻር የሚኖር የዋጋ ውድነት፤ የተጠቃሚውን የመግዛት አቅምና ግንዛቤ እንዲሁም ሌሎችንም የገበያ ባህሪ መለኪያዎችን እንደመነሻነት በመጠቀም የገበያ ዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል::

2. በኤጀንሲው ተገዝተው የሚቀርቡ አዳዲስ መድሃኒቶች፤ በግንዛቤና መረጃ እጥረት ምክንያት ለህሙማን የማይታዘዙ እንዲሁም አዝጋሚ እንቅስቃሴ የሚታይባቸውን መድሃኒቶች ዙሪያ መረጃ በማደራጀት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለሚለመከታቸው ተደራሽ ያደርጋል::

3. በተ.ቁ 1 እና 2 የተለዩትን የገበያ ስጋቶች ዋና ዋና መነሻ ምክንያቶችን ይለያል፣ ይተነትናል እንደአስፈላጊነቱም ችግሮችን እንደ ክብደታቸው ቅድሚያ መፈታት ያለባቸውን በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ አማራጮችን ይፈትሻል፤ የተሻለውን በመምረጥ እንደ አስፈላጊነቱ ነባራዊ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ማስተካከያ ያደርጋል እንዲሁም ምክረ ሀሳብ ያቀርባል::

4. የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችን በማስተባበር የተመረጠውን የመፍትሄ አማራጭ ይተገብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል ውጤቱን መሰረት ያረገ የእርምት እርምጃ ይወስዳል::

## ክፍል ሰባት

## የክትትልና ግምገማ ስርዓት

## 17. የክትትልና ግምገማ ስርዓት

1. ክትትልና ግምገማ የሚያስፈልጋቸዉን በስራ ሂደቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ይለያል፤ ተግባራቱን ለመለካት የሚያስችሉ ቁልፍ የአፈጻፀም መለኪያዎችን ያዘጋጃል፣ይከልሳል እንዲሁም መለኪያዎችን በመጠቀም ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችል የመነሻ የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል::

2. በአገር አቀፍ የመድሃኒት፣የህክምና መገልገያዎችና የራቦራቶሪ ሪኤጀንቶችና ኬሚካልስ የፍላጎት ትንበያ ስራዎች በየወቅቱ እየተሻሻሉ እንዲሄዱ መለኪያዎችን በማዉጣት በታቀደ የጊዜ ሰሌዳ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይገባል::

3. ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎችን በመጠቀም በትግበራዉ የተገኘዉን ዉጤት ይለካል ፣ የልኬቱን ዉጤት ከመነሻ የዳሰሳ ጥናቱ ጋር በማነፃፀር ይተነትናል፣ያደረጃል፤ ዉጤቱን መሰረት ያደረገ ማስተካከያ ያደርጋል እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸዉ አካላት ማሳወቅና ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፤ የክትትልና ግምገማ ሂደቱን ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያደርገል፤

4. የመደበኛም ሆነ የጤና ፕሮግራም ግብዓቶች ትንበያ የትክክለኛነት በመጠን (Forecasting accuracy by quantity) እንዲሁም በገንዘብ (Forecasting accuracy by value) ያሰላል፣ በየደረጃው ለትንበያ የሚያገለግሉ መረጃዎችን ጥራት ትክክለኛነት፣ ወቅታዊነትና ሙሉነት ይለካል (Quality of data by accuracy, timeliness and completeness)፣ በአገር አቀፍና በየደረጃው የኤጀንሲው መጋዘኖች ያለውን የመድሃኒት ብክነት መጠን ያሰላል (Wastage rate) ... ወዘተ በአፈጻጸም ዝቅ ያሉትን በመለየት ተገቢውን ድጋፍና ምክረ ሃሳብ ያቀርባል::

5. በተራ ቁጥር 17(4) የተገለጹ መለኪያዎችን ለማስላት ኤጀንሲው ለሁሉም የስራ ክፍሎች በሚያዘጋጀው ዝርዝር እቅድ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል::

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 18. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 19. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፡-

ይህ መመሪያ በኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡